የማኒቶባ የክልል
ሪፖርት ካርድ

መረጃ

# ለወላጆች

ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍሎች




Manitoba

*የማኒቶባ ትምርት ለሁሉም የትምርት ክፍፍሎች፡ በ2013/2014 የትምርት ዘመን የግድ መጠቀም ያለባቸው የክልል ሪፖርት ካርድ መጠቀም ጀምሯል፡፡*

# አጠቃላይ

## ለምንድነው አዲስ የሪፖርት ካርድ የተፈለገው?

የማኒቶባ መንግስት በማኒቶባ ውስጥ ያለው የትምህርት ጥራት ለማሻሻልና በተማሪዎች፣ አስተማሪዎቻቸውና ወላጆቻቸው መካከል ጠንካራ ግኑኙነት ለመገንባት አዲስ የሪፖርት ካርድ መጠቀም ጀምሯል፡፡

ቀደም ሲል፣ የሪፖርት ካርዶች በየንዳንዱ የትምርትቤት ክፍፍል እንዲሁም፣ በተወሰኑ ኣጋጣሚዎች፣ በአንድ ዓይነት ክፍፍል የሚገኙ ትምህርት ቤቶች የተለያዩ ነበሩ፡፡ ይኽ አዲስ የክልል ሪፖርት ካርድ፡ ወላጆች ልጆቻቸው ምን ያክል በጥሩ ሁኔታ እየተማሩ ናቸው፣ የመማር ሂደት እንዲሻሻል ምን ዓይነት እርምጃዎች ናቸው እገዛ የሚያደርጉት በሚሉት ጉዳዮች ላይ የማይለወጥና፣ ግልጽ መረጃ ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ የሚረዳ እዩ፡፡

## የሪፖርት ካርዱ ለመረዳት ቀላል ይሆናል ወይ?

የሪፖርት ካርዱ በቀላል ቋንቋ የተፃፈ ነው፡፡ የልጅዎ ጠንካራ ጎን እንዲሁም ልጅዎ ምን ላይ ነው እገዛ የሚያስፈልገው ይነግርዎታል፡፡ ስለዚህ የሪፖርት ካርድ ጥያቄዎች ካልዎት፣ የልጅዎን

አስተማሪ ማነጋገር ይችላሉ፡፡

## የሪፖርት ካርዱ ለሁሉም የክፍል ደረጃዎች አንድ ዓይነት ነውን?

ሶስት ዓይነት የሪፖርት ካርድ ቅርጾች ኣሉ፡፡ ኣንዱ ከ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍል፣ ኣንዱ ከ7ኛ እስከ 8ኛ ክፍል እንዲሁም ሌላው ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ናቸው፡፡

## በሪፖርት ካርዱ ላይ ያስተማሪ አስተያየቶች ይኖራሉን?

አዎን፡፡ አስተማሪዎች ልጅዎ በትምርትቤት ስለሚያሳየው ውጤትና ፀባይ አስተያየታቸውን ይጽፋሉ፡፡ እነዚህ አስተያየቶች ልጅዎ እንዴት እየሄደ ነው እንዲሁም እንዴት የልጅዎ የመማር ሂደት ማገዝ ይቻላል ለመረዳት ያግዝዎታል፡፡

## ልጄ እንዴት ነው የሚገመገው?

የትምርት ስኬት ውጤቶች ተማሪዎች የስርዓተ-ትምርት የመማር ዓላማዎች ምን ያክል በጥሩ ሁኔታ እያሳኩ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ይኽ ደግሞ መስፈርት-ያጣቀሰ የውጤት አሰጣጥ በመባል ይታወቃል፡፡ የትምርት ስኬት ውጤቶች፡ ልጅዎ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በማነጻጸር እንዴት እየሰራ ነው በሚል የተመሰረቱ ኣይደሉም፡፡ አስተሳሰብ፣ ጥረትና ፀባይ የመሳሰሉ ምክንያቶች ከትምርት ስኬት ተነጥለው ሪፖርት ይደረጋሉ፡፡ እነዚህ ምክንያቶች በትምርት ስኬት ብሎም ውጤቶች ላይ ተፅኖ የሚያሳድሩ መሆናቸው ግልፅ ሆኖ እንዳለ፣ በተናጠል ሪፖርት መደረጋቸው ለወላጆች የልጃቸው ጠንካራ ጎኖችና ማሻሻል ስለ ሚቻልባቸው ዙርያዎች የበለጠ መረጃ ይሰጣል፡፡

አስተማሪዎች ተማሪዎች ያላቸው ክህሎቶች እና አንድን የትምርት ዓይነት የመረዳት ችሎታ እንዲያሳዩ በርካታ መንገዶች ያዘጋጅሏቸዋል፡፡ የስኬት ውጤቶች ባጠቃላይ የልጅዎ በጣም የቅርብ ግዜ እንዲሁም የማይለወጥ የትምርት ስኬት ያንፀባርቃሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ይህ ማለት ደግሞ በአንድ ሴመስተር መጀመርያ ላይ በተሰጠ የቤት ስራ ላይ የተገኘ ዝቅተኛ ውጤት፡ በሴመስተሩ መጨረሻ የልጆዎ ውጤት በሚገመገምበት ወቅት፡ እሱ/ሷ በዛ ዙርያ የበለጠ መረዳት ወይም ክህሎት ካገኘ/ኘች ግምት ውስጥ ላይገባ ይችላል፡፡

## ውጤቶች እንዴት ነው ሪፖርት የሚደረጉት?

የተማሪ ውጤቶች በመቶኛ በማስላት ነው ሪፖርት የሚደረጉት፡፡

## ልጄ በትምርት ዓይነት ሊወድቅ ይችላልን?

አዎን፡፡ በ9ኛና 12ኛ ክፍሎች(ሁለተኛ ደረጃ)፣ ውጤቶች የሚሰጡት በክልሉ ስርዓተ-ትምርት የተቀረጹ፡ የመማር ውጤቶች መሳካት ማረጋገጫ ላይ በመርኮዝ ነው፡፡ ከ50% በታች የሆነ የመጨረሻ ውጤት፡ ተማሪው ያንን የትምርት ዓይነት

ለማለፍ በቂ ዕውቀትና ችሎታዎች ኣላሳየም ማለት ነው፡፡

## የሪፖርት ካርዱ መቼ ነው ወደ ቤት የሚላከው?

በትምርት ዘመን ኣጋማሽ/ሴመስተር ከፋፍለው በሚሰሩ ትምርትቤቶች፣ የሪፖርት ካርዶች በአንድ ሴመስተር ሁለቴ ወደ ቤት ይላካሉ፡፡ በሴመስተር ከፋፍለው በማይሰሩ ትምርትቤቶች ግን በመፀው፣ በፀደይና በትምርት ዘመን መጨረሻ ወደ ቤት ይላካሉ፡፡

## በሌሎች ግዜያቶች ካስተማሪዎች መረጃ ኣገኛለውን?

አዎን፡፡ ሪፖርት ካርዱ ከወላጆች ጋር የሚያገናኝ ኣንዱ መንገድ ብቻ ነው፡፡ ሌሎች ዘዴዎች፣ ስልክ መደወል፣ ስርዓት ያልተከተለ የዕድገት ሪፖርቶች፣ የወላጅ-አስተማሪ ስብሰባዎች፣ በተማሪ-የሚመሩ ጉባኤዎች፣ እንዲሁም የትምርት ቤት መፅሄቶች ያጠቃልላሉ፡፡

## የልጄ የትምርት ቤት ውጤት ካሳሰበኝ ምን ማድረግ ኣለብኝ?

የልጅዎን አስተማሪ ያነጋግሩ፡፡ ለልጅዎ አስቸጋሪ በሆኑባቸው የትምርት ዙርያዎች ዝርዝር ማዘጋጀት ኣጋዥ ይሆናል፡፡ ልጅዎ ስኬታማ እንዲሆን እንዴት በጋራ መስራት እንደሚችሉ አስተማሪውን ያነጋግሩ፡፡



*በዚህ ሰነድ ላይ፣ ወላጆች የሚል ቃል ለወላጆች ወይም አሳዳጊዎች የሚገልጽ ነው፡፡*

# የተማሪ ፕሮግራም አወጣጥ

የልጅዎ ፕሮግራም አወጣጥ፡ ልጅዎ በክፍል ደረጃ የተመረኮዘ ስርዓተ-ትምርት ይከተላል/ትከተላለች ወይስ ኣይከተልም/አትከተልም፣ ወይም ለመማር የሚያስፈልገው/የሚያስፈልጋት ነገሮች በበለጠ ለሟሟላት በልዩ ሁኔታ የተነደፈ ሌላ የፕሮግራም አወጣጥን ይገልጻል፡፡

ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል(ሁለተኛ ደረጃ)፣ የትምርት ዓይነቶች ሶስት አሃዝ/ፊደል ያለው ቁጥር ያሰጣጥ ዘዴ ይጠቀማሉ፡፡ ሶስተኛው አሃዝ/ፊደል (ለምሳሌ፣20F – "F"፣ በዚህ ምሳሌ) ልጅዎ የሚከተለው የፕሮግራም አወጣጥን ያመለክታል፡፡ ልጅዎ በአንድ የትምህርት ዓይነት፡ በክፍል-ደረጃ የተመረኮዘ ስርዓተ-ትምርት እየተከተለ ከሆነ፣ የሪፖርት ካርዱ ከሚከተሉት ፊደሎች ኣንዱን ይጠቀማል፡፡

F (መሰረት)፣ S (ልዩ) ወይም G (አጠቃላይ)፡፡

ልጅዎ በአንድ የትምርት ዓይነት፡ በክፍል-ደረጃ የተመረኮዘ ስርዓተ-ትምርት እየተከተለ ካልሆነ፣ የሪፖርት ካርዱ ከሚከተሉት ሶስት የፕሮግራም አወጣጥ ዓይነቶች (እንዲሁም ተዛማጅ የፊደል ኮዶች) እንደሚጠቀም ያመለክታል፡፡



## 1. M የፕሮግራም አወጣጥ

"M" ባይምሯዊ(ከግኒቲቭ) ኣካለ-ጎዶሎነት ምክንያት አስፈላጊ የሚሆን የፕሮግራም አወጣጥን ይገልጻል፡፡ ይህ ተማሪ በሪፖርት ካርዱ ላይ የሚያገኛቸው ውጤቶች፡ ለተጠቀሰው ተማሪ የሚስማማ የመማር ዓላማዎች የሚያመለክቱ ናቸው፣ እንደዚሁም እነዚያ ዓላማዎች በግለሰቡ የትምርት ዕቅድ (IEP) በግልጽ ተዘርዝሯል፡፡

## 2. E የፕሮግራም አወጣጥ

"E" ለኢንግሊዘኛ እንደ ተጨማሪ ቋንቋ (EAL) የፕሮግራም አወጣጥን ያመለክታል፡፡  አንድ ተማሪ በመጀመርያ ኢንግሊዘኛ እንደ ተጨማሪ ቋንቋ የመማር መድረኮች ላይ፣ የትምርት ዓይነቱን የሚመለከት የኢንግሊዘኛ ቋንቋ በመማር ላይ ያተኩራል፡፡ ይህ ተማሪ በሪፖርት ካርድ ላይ የሚሰጡት ውጤቶች፡ ከተጠቀሰው ተማሪ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ዕውቀት ደረጃ ጋር የሚስማማ፡ በቋንቋና በየትምርት ዓይነት የመማር ዓላማዎች መካከል የሚኖር መመዛዘን ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡ እነዚያ ዓላማዎች በተማሪው የEAL የትምርት ዕቅድ ላይ በግልጽ ተዘርዝሯል፡፡

## 3. L የፕሮግራም አወጣጥ

"L" የፈረንሳይኛ የመጻፍና ማንበብ መቻል የፕርግራም አወጣጥን ያመለክታል፣ እንዲሁም ለፈረንሳይኛ ፕሮግራም እና ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል የሚመለከት የፍሬንች ኢመርሽን ፕሮግራም ይመለከታል፡፡ የክልል ስርዓተ-ትምርቱ ስኬታማ በሆነ መንገድ ለመከተል፣ የፈረንሳይኛ ቋንቋ ችሎታው ለማሳደግ ተጨማሪ እገዛ የከሚያስፈልገው ተማሪ፡ በትምርት ዓይነት በመርኮዝ ፈረንሳይኛ በመማር ላይ ሊያተኩር ይችላል፡፡ ይህ ተማሪ በሪፖርት ካርዱ ላይ የሚያገኛቸው ውጤቶች፡ ከተጠቀሰው ተማሪ የቋንቋ ችሎታ ደረጃ ጋር የሚስማሙ፡ በቋንቋና የትምርት ዓይነት የመማር ዓላማዎች ያለ መመዛን ላይ የሚመረኮዝ ነው፡፡ እነዚያ ዓላማዎች በተማሪው በፈረንሳይኛ የመጻፍና የማንበብ የትምርት ዕቅድ ላይ በግልጽ ተዘርዝሯል፡፡

ከታች የተቀመጠው ናሙና፣ የፕሮግራም አወጣጥ ዓይነት በቀይ ክብ ተመልክቶ ሊያዩት ይችላሉ፡፡ በዚህ ምሳሌ ላይ፣ ተማሪው ለሂሳብ የትምርት ዓይነት በተመለከተ የተሻሻለ የ("M") ፕሮግራም አወጣጥ እየተከተለ ነው፡፡

| | Attendance and Achievement | | | | | | | | Learning Behaviours | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | Term 1 | | | Term 2 | | | Final | | Term 1 | | | Term 2 | | |
| | Lates | Absences | Grade | Lates (Total) | Absences (Total) | Grade | Final exam | Final grade | Personal management skills | Active participation in learning | Social responsibility | Personal management skills | Active participation in learning | Social responsibility |
| Semester:<br>Teacher:<br>Credit Value:<br>Credits Earned: | Course: **Mathematics 10M** | | | | | | | | | | | | | |
| | | | % | | | % | % | % | | | | | | |
| | Comments: | | | | | | | | ❑ IEP (behaviours) | | | | | |

# የክልል የሚጠበቁ ነገሮችን የሚያመለክት የትምርት ስኬት

መቶኛ የውጤት መለኪያ፡ በተማሪዎች የውጤት ካርዶች ላይ የያንዳንዱ የተወሰደ የትምርት ዓይነት አጠቃላይ ውጤት ለማየት ይጠቅማል፡፡ከታች የተጠቀሰው ቻርት የመቶኛ የውጤት መለኪያ እንዴት በትምርት ዓይነቱ ላይ ከትምርት-ነክ ስኬት ጋር ይዛመዳል፣ እንዲሁም ሌሎች የተጠቀሱ ኮዶችን ያሳያል፡፡ ለ11ኛና 12ኛ ክፍሎች የሚሰጥ የአካል ብቃት/የጤና ትምርት የሚመለከቱ የትምርት ዓይነቶች፣ መቶኛ የውጤት መለኪያ እንደማይጠቀም ያስተውሉ፡፡ በምትኩ ግን፣ **CO** እንዲሁም **IN** የሚባሉ፣ ከላይ የተጠቀሱ ኮዶች በሪፖርት ካርዶቹ ላይ ይጠቀማሉ፡፡



| Academic Achievement of Provincial Expectations | Percentage Grade |
|---|---|
| Very good to excellent understanding and application of concepts and skills | **80% to 100%** |
| Good understanding and application of concepts and skills | **70% to 79%** |
| Basic understanding and application of concepts and skills | **60% to 69%** |
| Limited understanding and application of concepts and skills; see teacher comments | **50% to 59%** |
| Does not yet demonstrate the required understanding and application of concepts and skills; students with a final grade of less than 50% are not granted course credit; see teacher comments | **Less than 50%** |
| **Additional Codes** | |
| **Course Complete:** Final passing grade for courses using CO/IN for grades, e.g., Grades 11 and 12 Physical Education/Health Education. | **CO** |
| **Course Incomplete:** Final grade showing insufficient evidence of learning for courses using CO/IN for grades, e.g., Grades 11 and 12 Physical Education/Health Education. May also be used in other courses but not as a final grade. | **IN** |
| No exam applies | **NE** |
| No mark for the school-based final exam or provincial test, where applicable | **NM** |

የሚቀጥለው ምሳሌ ኣንድ የ10ኛ ክፍል የሳይንስ ትምርት፡ መደበኛ በክፍል-ደረጃ ላይ የተመረኮዘ ስርዓተ-ትምርት የፕሮግራም አመዳደብ የሚወስድ ተማሪ የሚያሳይ ነው፡፡ በተጨማሪ ሶስቱ፣ ከታች የጠቀሱ፣ የመማር ፀባዮች ያሳያል፡፡ ከመጨረሻው ውጤት 20% ያክል የሚሸፍነውን የመጨረሻ ፈተናን ያካትታል፡፡

| | **Attendance and Achievement** | | | | | | | | **Learning Behaviours** | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | **Term 1** | | | **Term 2** | | | **Final** | | **Term 1** | | | **Term 2** | | |
| | Lates | Absences | Grade | Lates (Total) | Absences (Total) | Grade | Final exam | Final grade | Personal management skills | Active participation in learning | Social responsibility | Personal management skills | Active participation in learning | Social responsibility |
| Semester: 1<br>Teacher: Ms Osmand<br>Credit Value: 1<br>Credits Earned: 1 | Course: **Science 20F** | | | | | | | | | | | | | |
| | 2 | 1 | 70% | 3 | 1 | 75% | 80% | 76% | C | U | S | U | S | C |
| | Comments: | | | | | | | | ❑ IEP (behaviours) | | | | | |

# ከሁለተኛ ደረጃ ትምርት መመረቅ

ከ9ኛ እስከ 10ኛ ክፍሎች (ሁለተኛ ደረጃ)፣ ተማሪዎች በያንዳንዱ የክፍል ደረጃ፣ ለያንዳንዱ የሚወስዱት የትምርት ዓይነት፣ 50% (ወይም በላይ) የማሳለፍያ ውጤት ካገኙ በኋላ፣ ለመመረቂያ የሚታሰቡ ውጤቶችን ያከማቻሉ፡፡

ለወላጆች ስለ መመርቂያ መመዘኛዎች የሚመለከት መረጃ በኢንተርነት በዚህ ድረገጽ ይገኛል፡-

**www.edu.gov.mb.ca/k12/policy/grad_require.html**

ለርስዎም ሆነ ለልጅዎ፡ ልጅዎ እያገኛቸው ያሉ ውጤቶች ለመመረቅ ያስችላሉን፣ እንዲሁም ልጅዎ ከምረቃ በኋላ የሚኖሩት ዕቅዶች ጋር የሚስማሙ መሆናቸውን የሚሉት ጉዳዮች ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡ የሪፖርት ካርዱ ልጅዎ ለመመረቅ እያሳየው ያለውን ዕድገት የሚያሳይ ሰንጠረዥ አለው፡፡ ይህን በተመለከተ በማንኛውም ግዜ ስጋቶች ካልዎት፣ ልጅዎ የሚማርበት ትምርት ቤትን ያነጋግሩ፡፡


# የመማር ፀባዮች

ትምርት-ነክ ስኬት ሪፖርት ከማድረግ በተጨማሪ፣ የሪፖርት ካርዶች ልጅዎ ክፍል ውስጥ የሚያሳየው ጥረትና አመለካከትን ያሳያል፣ ቀደም ሲልና ከታች እንደተገለጹትና እንደተጠቀሱት ምሳሌዎች እንደምናየው፣ "የመማር ፀባዮች" ከሚለው ስር ተገልጿል፡፡ በዚህ ክፍል የሚገኝ የIEP ሳጥን፡ ልጅዎ ከመማር ፀባዮች ጋር የሚዛመዱ ዓላማዎች ያቀፈ የግል የትምርት ዕቅድ ካለው ተግባራዊ ይሆናል፡፡

| **Learning Behaviours** | |
|---|---|
| **Scale** | **C**: Consistently – almost all or all of the time<br>**S**: Sometimes – less than half of the time<br>**U**: Usually – more than half of the time<br>**R**: Rarely – almost never or never |
| **Personal management skills** | Uses class time effectively; works independently; completes homework and assignments on time |
| **Active participation in learning** | Participates in class activities; self assesses; sets learning goals |
| **Social responsibility** | Works well with others; resolves conflicts appropriately; respects self, others and the environment; contributes in a positive way to communities |

የመማር ፀባዮች በቀጥታ በተማሪዎች ውጤቶች ላይ የሚካተቱ ኣይደሉም፣ ሆኖም ግን፣ በትምርት-ነክ ስኬታቸው ላይ ጫና ሊያሳርፉ ይችላሉ፡፡ ጠቃሚ የመማር ፀባዮች ማሳደግ፡ በትምርት ቤትም ሆነ ውጭ በህይወታቸው ላይ ለውጥ እያመጡ በምሄዱበት ወቅት፡ ለመጪው ግዜ ለተማሪዎች ለውጥ ሊያመጣላቸው ይችላል፡፡ ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው ከሰሩ፣ ተነሳሽነት ካሳዩ፣ እንዲሁም የመማርያ ክፍል ክብሮችን ካከበሩ፣ እነዚህ ክህሎቶች በተለያዩ ሌሎች የህይወታቸው ዘርፎች ላይ ሊጠቀሙቧቸው ይችላሉ፡፡

በፍሬንች ኢመርሽን ፕሮግራም ተሳታፊ ለሆኑ ተማሪዎች፣ የተማሪዎች የፈረንሳይኛ ቋንቋ አጠቃቀም ተግባርን በተመለከተ የመማር ጸባይ አለ፡፡



# ለተጨማሪ መረጃ

ለተጨማሪ መረጃ የማኒቶባ ትምርት ድረገጽን ይጎብኙ፡

- ልጅዎ **በተለያዩ የትምርት ዓይነት ዙርያዎች** ላይ ምን እየተማረ እንደሆነ ለመረዳት፡-
  www.edu.gov.mb.ca/k12/cur/parents/ (የእንግሊዘኛ ፕሮግራም)
  www.edu.gov.mb.ca/k12/cur/parents/fr_imm/ (የፈረንሳይኛ ኢመርሽን (Immersion) ፕሮግራም)
  www.edu.gov.mb.ca/m12/progetu/parents/ (የፈረንሳይኛ ፕሮግራም)
- **ተማሪን ለመመርመር** የተዘጋጁ ፖሊሲዎችና መመርያዎች፡-
  www.edu.gov.mb.ca/k12/assess/
- **የክልል ሪፖርት ካርድ**፡-
  www.edu.gov.mb.ca/k12/assess/report_cards/index.html

# የምትጨምሩት ነገር በደስታ እንቀበላለን

ወላጅ ወይም አሳዳጊ፣ አስተማሪ፣ ተማሪ ወይም ፍልጎት ያለው የማህበረሰብ አባልም ይሁኑ፣ ለዚህ አዲስ የሪፖርት ካርድ ያልዎት ምላሽ አስፈላጊ ነው፡፡ ባጠቃላይ፣ ሪፖርት ካርድ ግልጽና መረጃ ሰጭ ሆኖ አገኙት ወይ? አሁንም ቢሆን መሻሻል ያለባቸው የሪፖርት ካርዱ ክፍሎች አሉን?

አስተያየትዎ ማቅረብ ከፈለጉ፣ እባክዎን ከታች ወደ ተገለጸው አድራሻ በፖስታ ይላኩት ወይም የተመለከተው የኢንተርኔት ድረ-ገፅ በመጎብኘት የኦንላይን የምላሽ መስጫ ቅፅ ሞልተው ይላኩ፡፡

| ምላሽ በፖስታ ይላኩ | ምላሽ በኦንላይን |
|---|---|
| *Provincial Report Card Feedback*<br>Manitoba Education<br>1567 Dublin Avenue<br>Winnipeg MB  R3E 3J5 | www.edu.gov.mb.ca/k12/assess/report_cards/feedback.html |



ጥያቄ ካቀረቡ በሌላ ዓይነት ቅርጾች/መልኮች ሊያገኙ ይችላሉ፡፡